# ሓወልቱ ይመስክር!

ፋሺስት ሞሶሊኒን ታሪክ ተፋረደው፣
ከመቃብር ሆኖ ወንጀሉ ከበደው!
ይህ ይመጣል ብሎ መች ገመቱና፣
ስልጣን አለኝ ብሎ አፍሪካን ቃኘና፣
በትዕቢት ሰማጠ፣ በምኞት ቋማጠ፣
ከሮማ ተነስቶ ባሕሩን አቋረጠ፣
ገብቶ በምጽዋ ፣ ተሻግሮ በአሥመራ፣
ጉልበት አለኝ ብሎ ሊዘርፍ ተሰማራ።

ቀን አይመጣ መስሎት፣ አይነጋ ሌሊቱ፣
በእጄ ነው ብሎ ጉልበቱ፣ ሰዓቱ፣
በቡጢ ሊማታ፣ ሊያወልቅ አንድ ጥርስ፣
የቱን ልስረቅ ብሎ ሚጠፍ ቅርስ
የኢትዮጵያን ታሪክ መዳፈር ቢያምረው፣
የአክሱምን ሓወልት ነቃቅሎ ወሰደው።

ግን ሌቱ ሲነጋ፣ ጉዱ ሲጋለጥ፣
ሌባው ተያዘና፣ ዓይኖቹ ፍጥጥ!
የተሠራው ሥራ ስሕተት ነው ተብሎ፣
ሓወልቱን ማለሰው ባየር አቀባብሎ፣
የዘመኑ ትውልድ ስሕተቱን አረመው፣
ከጥንቱ፣ ከቦታው አምጥቶ አቆመው።

እንግዴህስ ዛሬ ከታሪክ መማር፣
ለኔ ጥቅም ብሎ ለራስ ከሚደር፣
ለሃገር የሚበጅ መቋጨት፣ ማሰር።
ስልጣን በእጄ ነው፣ ማን አለብኝ ብሎ
በምላስ ጮሌነት ሰውን አታልሎ፣
ሓቅና ሓሰቱን ተንኮሉን ቀላቅሎ፣
ምን ቢሸፋፍኑት በጨርቅ ተጠቅልሎ
እውነቱ ይወጣል በውን አድሮ ውሎ!

ስልጣን ሓላፊ ነው፣ ጉልበትም ይከዳል፣
መጪው ትውልድ ግን ሁሉንም ይፈርዳል!
መዓርግ ቀሪ ነው፣ ዝናም ሁሉ ያልፋል፣
መልካም ሥራ ብቻ ለታሪክ ይተርፋል፣
አርቆ መመልከት ያሻል በዘመኑ፣
ታሪክ ነው መለኪያው፣ ለሁሉም ሚዛኑ።

ገ/ኢ. ጐርፉ።
April 2005